# የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
# COMMERCIAL BANK OF ETHIOPIA

## Merkato District

### የጨረታ ማስታወቂያ
### በድጋሚ የወጣ የተለያዩ ያገለገሉ ንብረቶች ጨረታ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መርካቶ ዲስትሪክት የተለያዩ ያገለገሉ የቢሮ መገልገያዎች (የፈርኒቸር እቃዎችን) እና ያገለገሉ ጎማዎችን ባሉበት ሁኔታ በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

1. ስለ አሻሻጡ የተዘጋጀውን ዝርዝር ሁኔታ የያዘውን ሰነድ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መርካቶ ዲስትሪክት መኮንን ቢ.ተወ. ህንፃ 6ኛ ፎቅ የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር ብቻ) በመክፈል ከመስከረም 25 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥቅምት 09 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10:00 ሰዓት ድረስ ባሉት የስራ ቀናት መውሰድ ይችላሉ፡፡

2. ተጫራች ያገለገሉ ንብረቶችን ከመስከረም 25 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ ጥቅምት 12 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አባኮራን ቅርንጫፍ 3ኛ ፎቅ እና አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቀጥር 210 ከጠዋቱ ከ2:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 6:00 ሰዓት ከሰዓት በኂላ ከቀኑ 7:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 10:00 ሰዓት ድረስ ባሉት የስራ ቀናት በመገኘት ማየት ይችላሉ፡፡

3. ተጫራች ለሚጫረትበት ላገለገሉ የንብረት ዓይነቶች የጨረታ የመነሻ ዋጋውን 25% (ሃያ አምስት በመቶ) የጨረታ ማስከበሪያ (Bid Bond) በባንክ ክፍያ ማዘዣ (CPO) ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መርካቶ ዲስትሪክት (Commercial Bank of Ethiopia Merkato District) በሚል ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

4. የተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ጥቅምት 13 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት ላይ ታዛቢዎች በተገኙበት ይታሸጋል፡፡

5. ተጫራች ለንብረቱ የሚሰጠውን ዋጋ ከጨረታ ሰነዱ ላይ ባለው ክፍት ቦታ በመሙላት የጨረታ ማስከበሪያ እና ሌሎችም አስፈላጊ ሠነዶችን በፖስታ በማሸግ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መርካቶ ዲስትሪክት መኮንን ቢ.ተወ. ህንፃ 6ኛ ፎቅ ላይ በተዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ማስገቢያ ሳጥን ውስጥ ጥቅምት 13 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 4:00 ሰዓት ብቻ ያስገባል፡፡

6. ጥቅምት 13 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 4:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው እንዲሁም ታዛቢዎች በተገኙበት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መርካቶ ዲስትሪክት መኮንን ቢ.ተወ. ህንፃ 6ኛ ፎቅ በግልጽ ይከፈታል፡፡

7. ለጨረታ ማስከበሪያ የተያዘው ገንዘብ አሸናፊ ለሚሆነው በሚገዛው ንብረት ክፍያ ላይ የሚታሰብ ሲሆን አሸናፊ ላልሆኑት ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

**ባንኩ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡**